## ስለ ስዊፍት የሐዋላ አገልግሎት ምን ያህል ያውቃሉ?

ስዊፍት ማለት ዓለማቀፍ የባንክ ማህበረሰብን በመረጃ መረብ በማገናኘት አባል ለሆኑ ባንኮችም ሆነ የፋይናንስ ተቋማት ቀልጣፋና አስተማማኝ የሆነ የመረጃ ልውውጥ የሚደረግበት ዘመናዊ ዘዴ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት የተጠቃሚዎች ቁጥር በመላው ዓለም ከ8000 በላይ ደርሷል፡፡

በስዊፍት የሚላኩ መረጃዎች ሚስጥራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በኮምፒውተር ቴክኖሎጂ በመታገዝ በቀላሉ ወደ ሚፈለግበት ሀገር እና ወደ ተጠቃሚው ድርጅት ወይም ግለሰብ በአፋጣኝ እንደሚደርሱ ጥርጥር የለውም፡፡

ብዛት ካላቸው የስዊፍት አገልግሎቶች መካከል አንዱ የሀዋላ አገልግሎት ሲሆን፣ ከተለያዩ የዓለም አቅጣጫዎች የተላከን ገንዘብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለደንበኞች እንዲደርስ የሚያደርግ እጅግ ተመጣጣኝ የሆነ የአገልግሎት ክፍያን የሚጠይቅ አስተማማኝ አገልግሎት ነው፡፡

### የስዊፍት የሐዋላ አገልግሎት የሚከተሉት ባህሪያት አሉት

❖ **ሚስጥራዊነት**

በስዊፍት የሚላኩ መልዕክቶች ሚስጢራዊነታቸው በከፍተኛ ደረጃ የተጠበቀ በመሆኑ አግባብ ያለው አካል ካልሆነ በቀር መረጃውን ማንም ቢሆን ሊያገኘው አይችልም፡፡

❖ **ቀላልና ምቹ መሆኑ**

ገንዘብ በስዊፍት አገልግሎት ለመላክ ረጅም የሆነ የአሠራር ሂደት ባለመኖሩ ደንበኞች በቀላሉ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ ደንበኞች የሚስጥር ቁጥር ወይም የገንዘብ መላኪያ ኮድ አያስፈልጋቸውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተላከልዎት ገንዘብ የቱንም ያህል ጊዜ ሳይወስዱት ቢቆዩ ወደላኪው ተመላሽ አይሆንም፡፡

❖ **አስተማማኝነቱ**

የስዊፍት የሐዋላ አገልግሎትን ሲቀጠሙ መልዕክቱ ሙሉ በሙሉ ዓለም አቀፍ ደረጃን በአሟላ ጥበቃ የተደገፈ በመሆኑ የሚላከው ገንዘብ በትክክል ለተፈለገው ተቀባይ እንደሚደርስ እርግጠኛ ይሁኑ፡፡

❖ **ፈጣንነቱ**

የስዊፍት አገልግሎት አባል የሆኑ ባንኮች በኮምፒውተር መረብ የተገናኙ ስለሆነ፣ መረጃዎችም ሆነ መልዕክቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደሚፈለጉበት አቅጣጫ ይሄዳሉ፡፡ በዚህ መሠረት ከውጭ ሀገር የተላከ ገንዘብ በአፋጣኝ ወደ ተቀባዩ ይደርሳል፡፡

❖ **እጅግ አነስተኛ ክፍያ**

ከሁሉም የውጭ ሐዋላ አገልግሎቶች ይልቅ እጅግ አነስተኛ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ የሚጠይቅ ይኸው የስዊፍት የሐዋላ አገልግሎት ነው፡፡ በርካሽነቱ የታወቀና ሁሉም ተጠቃሚ የሚገረምበት ነው፡፡

❖ **ገንዘብ ላኪዎች ማወቅ የሚገባቸው ቁምነገሮች**

- የተቀባዩን ሙሉ ስም/ከነአያት/ እንዲሁም አድራሻ፣
- የተቀባዩን የባንክ የሂሳብ ቁጥር /ተቀባዮች፣ የባንክ ሂሳብ ቢኖራቸው የሚላክላቸው ገንዘብ በቀጥታ ወደ ሂሳባቸው ገቢ ስለሚደረግ ጊዜንም ሆነ ጉልበትን ይቆጥባል/፣
- ለተቀባዩ ቅርበት ያለውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ፣
- የተቀባዩ የባንክ መለያ ቁጥር /Bank identifier code/፣
- የተቀባዩን ሀገር እንዲሁም ከተማ፣
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የስዊፍት አድራሻ ማለትም CBETETAA፡፡

❖ **ተቀባዮች የሚከተሉትን ነጥቦች ልብ ይበሉ**

- ገንዘብ ለሚልክላቸው ግለሰብ ሙሉ ስም ከነአያት፣ በአቅራቢያቸው ያለውን ቅርንጫፍ፣ የባንክ ሂሳብ ካላቸው የሂሳብ ቁጥራቸውን፣ የባንኩን የስዊፍት አድራሻ፣ እንዲሁም አድራሻቸውን ከነስልክ ቁጥራቸው በትክክል መስጠታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፣
- ገንዘብ ሊወስዱ በሚመጡበት ወቅት የመታወቂያ ካርድ /የቀበሌ፣ መንጃ ፈቃድ ወይም ፓስፖርት/ ይዘው መምጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- ምንም ዓይነት ክፍያ አይጠበቅባቸውም፡፡

ስል ስልክ 251-11-5519506
ፋክስ. 251-11-5546243

የመ.ሣ.ቁጥር 255 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ኢሜል: cbeftnrt@ethionet.et
ዌብ ሳይት: www.combanketh.com
ስዊፍት፡ CBETETAA

# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

**ለፍላጎትዎ መሟላት**
**የሚተማመኑበት!**